# መርዛማ የወያኔ/ኢ.ሕአዴግ የዘር ፖለቲካን እናምክን !
# አንድነት (መድረክን) እንደግፍ !

(amanuelzeselam@gmail.com)
አማኑዔል ዘሰላም

ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ኢ.ሕአዴግ ስልጣን በጨበጠ በአሥራ ስድስት ወራቱ ነዉ አገሬን ለቅቄ የስደት ኑሮ የጀመርኩት። በማውቃቸዉ የአሥራ ስድስት ወራቱ የኢ.ሕአዴግና የኦነግ የጋራ አገዛዝ፣ የባንክ ሰራተኞች ያለምንም ርህራሄ ሲባረሩ፣ በበደኖና በአርባ ጉጉ «ነፍጠኞች» እየተባሉ ኢ.ትዮጵያዉያን በግፍና በጭካኔ ሲገደሉ አስታወሳለሁ። በድሬደዋ ከተማም ለሶስት ቀናት ተቀስቅሶ የነበረዉ የዘር ግጭት በዚ.ያ ወቅት ነበር የተከሰተዉ።

ያኔ ኢ.ሕአዴግ ለሚያካሂደዉ የክልል ምርጫ በየቀበሌያችን መመዝገብ ነበረብን። ወደ ቀበሌዬ ልመዘገብ ሄድኩኝ። ስሜን ጠይቁኝና ነገርኳቸዉ። መዝገቡ ላይ ጻፉ። ብሄሬን ጠየቁኝ። «ኢ.ትዮጵያዊ» አልኳቸዉ። «አይደለም፣ እርሱማ ሁላችንም ኢ.ትዮጵያዊያን ነን። ማለታችን አማራ ነህ፣ ኦሮሞ ....? » ብለዉ ደግመዉ ጠየቁ። «እርሱን መመለስ አልችም። አላዉቀዉም።» አልኳቸዉ። «አባትህ ምንድናቸዉ ? » አሉኝ። «አባቴ እርሱም አዲስ አበባ እንደተወለደ ነዉ የማውቀዉ። ዘሩን አላውቅም» አልኳቸዉ»። ሊመዘግቡኝ አልቻሉም። አማራ ወይንም ትግሬ ወይንም ኦሮሞ ወይንም አንዱን ዘር ካልመረጥኩኝ በኢ.ትዮጵያዊነቴ የመምረጥ መብት እንደሌለኝ ተነገረኝ። ሳልመዘገብ ወደ ቤቴ ተመለስኩኝ።

ከአሥራ አራት አመት ስደት በኋላ ወደ አገሬ በተመለስኩኝ ጊዜ የተለወጠ ነገር እንደሌለ አስተዋልኩ። እያንዳንዱ ኢ.ትዮጵያዊ መታወቂያዉ ላይ ዘሩን ካልጠቀሰ መታወቂያ አይሰጠዉም። አንድ ሰዉ መታወቂያ ካላገኘ ማንነቱን የሚገልጽ ነገር የለዉም ማለት ነዉ። በሌላ አባባል አንድ ሰዉ «ትግሬ ነኝ። ኦሮሞ ነኝ። አማራ ነኝ ..» ካላለ በኢ.ትዮጵያ ዉስጥ «ምንም» እንዳልሆነ ያሳያል።

አንድ በናዝሬት ተወልዶ ያደገ ወዳጄ የነገረኝን ታሪክ ላጫዉታቹህ። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ይምረቃል። በናዝሬት የክልሉ አስተዳደር ዉስጥ በተማረበት ሞያ፣ ለመሥራት ያመለክታል። ሁሉንም ነገር ካጠናቀቀ በኋላ ሊቀጠር እንደማይችል ይነገረዋል። ምክንያቱን ሲጠይቅ «ኦሮሞ ስላልሆንክ፣ በኦሮሚያ መቀጠር አትችልም» ነበር ያሉት። ሥራዉን ለማግኘት «እኔ ኦሮሞ ነኝ» ብሎ ተከራከረ። «መታወቂያህ ላይ አማራ ነዉ የሚለዉ። አስለዉጥ» አሉት። መታወቂያዉን አስለወጠ። መታወቂያዉ ላይ አማራ የሚለዉን ወደ ኦሮሞ አስቀየረ። ስራዉን አገኘ። (ይህ ሰዉ ኦሮምኛም ስለሚናገርና ስለሚጽፍ በቀላሉ አማራን ወደ ኦሮሞ በመቀየር ተገላገለ። ግን አንድ ኦሮሞ ነኝ የሚል በኦሮሚያ ያደገ ሰዉ ቢ.ሆን ኖሮ፣ ትምህርት ቤት በቁቤ ስለሚማር፣ ምናልባትም አማርኛ መጻፍ ሊከብደዉ ይችላል። በመሆኑም በሌላዉ ክልል ሥራ የማግኘቱ እድል ባዶ ይሆን ነበር)

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋሟት በቀዳሚነት የኢ.ትዮጵያን

ሕዝብ ብሶት ማንጸባረቅና አገዛዞች የሚያራምዱትን ጎጂ ፖሊሲዎች በመቃወም ነበር የሚታወቁት።

አሁን ግን ከተቋማቱ የምናየዉ ተማሪዎች እርስ በርስ በዘር ላይ የተመሰረተ ግጭት ሲፈጥሩ ነዉ። በአለማያ (አሁን ሃረማያ ተብሏል) ፣ በባሀር ዳር፣ በጂማ እንዲሁም በበርካታ ተቋማት ብዙ ጊዜ በሴንጢ እስከመገዳደል የደረሰ የተማሪዎች ብጥብጥ እየተነሳ፣ የፌደራል ፖሊስ ጣልቃ የገባበት ጊዜ ብዙ ነዉ። (እንግዲህ አስቡት በዚህ ሁሉ ግርግር «ጥሩ አካል» ሆኖ እየታየ ያለዉ የፌደራል ፖሊስ ነዉ።)

ዉድ ወገኖቼ ፤

ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉ እዉነታ ይሄ ነዉ። እኔ እንደማስበዉ የኢትዮጵያ ትልቁና ዋናዉ ችግር ይሄ ነዉ። ይህ ችግር የኢትዮጵያ ሕልዉና ላይ ያተኮረ ችግር ነዉ። ይህ ችግር በአስቸኳይ ምላሽ ካልተሰጠዉ ወደፊት ኢትዮጵያ የምትባል አገርም ላትኖረንም ትችላለች።

ለዚህም ነዉ የኢትዮጵያ የተቃዉሞ ፖለቲካ፣ ለዚህ ትልቅ የአገራችን ችግር መፍትሄ በማምጣት ዙሪያ መመስረት አለበት ብዬ አጥብቄ የማምነዉ። ለዚህም ነዉ በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመራዉ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፣ የብሄር ፖለቲካ ያራምዱ የነበሩትን፣ ወደ ሕብረ ብሄራዊነት እንዲመጡ በማድረግ ዙሩያ እያደረገ ያለዉን ቁልፍ እንቅስቃሴ በጣም መሰረታዊ፣ እጅግ ጠቃሚና በሰፋት ሊደገፉ የሚገባዉ አድርጌ የምወስደዉ።

የከንባታ ህዝቦች ኮንግረስ በብሄር ላይ የተመሰረተዉን ድርጅታቸዉን አፍርሰዉ የአንድነት ፓርቲን ተቀላቅለዋል። ሌሎችም የጎሳ ድርጅቶች በቅርቡ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ሥር፣ የአንድነት ፓርቲን እንደሚቀላቀሉ የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች እያየን ነዉ።

የኦሮሞ ነጻ አዉጭ ግንባርን እስተሳሰብ ያራምዳሉ ተብለዉ ሲተቹ የነበሩት፣ ዶር ነጋሶ ጊዳዳ «ለኦሮሞዉም ሆነ ለተቀረዉ ኢትዮጵያዊ የሚበጀዉ በአንድነትና በሀብረ ብሄራዊነት መታገል ነዉ» ብለዉ የአንድነት ፓርቲ አባል፣ አልፎም የአመራር አባል ሆነዋል።

በ1991 የተከበሩ ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየሱስ ብቸኛ ተቃዋሚ በነበሩበትና ቻርተሩ በጸደቀበት በአዲስ አበባ ኮንፍራንስ ላይ፣ ያኔ የሕወሃት ተወካይ የነበሩት፣ አቶ ስዬ አብርሃ ፣ የብሄር ብሄረሰብ መብት እስከ መገንጠል የሚለዉን ሲያብራሩ የማእዘን ድጋይ አድርገዉ ነበር ያቀረቡት።

አሁን አቶ ስዬ፣ የሁሉ ነገር መሰረት ወይንም የ«ማእዘን ድንጋይ» አድርገዉ የሚወስዱት የግለሰቦችን ነጻነት ነው። በግለሰቦች ነጻነት ዉስጥ የቡድን መብት ይከብራል ብለዉ የሚያምኑ ናቸዉ። «ኢትዮጵያዉያን በዘርና በጎሳ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ጥላ ሥር ተሰባሰበን፣ ለሁሉም እኩል የሆነችን ኢትዮጵያ መገንባት አለብን» የሚል ጠንካራ አቋም በመያዛቸዉ፣ የብርቱካን ሚደቅሳን ፓርቲ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲን

ተቀላቅለዋል።

ከላይ እንደጠቀስኩት አገራችን አደጋ ላይ ናት። አገራችንን ማዳን ይጠበቅብናል። አገራችንን የምናድነዉ በዘርና በኃይላኖት በመከፋፈል፣ ያለፈዉን በጥላቻ በማንሳት፣ የስድብና የዉሸት ፖለቲካን በማስፋፋት፣ ምንም ሳንይዝ በዜሮ ድምር የዘራፍ ፖለትካ በመጠመድ፣ የሚገዙትን ሕዝብ እያረዱ ያሉትን እንደ ሻአቢያ አይነቶቹ ላይ በመደገፍ አይደለም።

አገራችንን የምናድነው እውነትን በመነጋገር፣ በራሳችን ህዝብ በመተማመን፣ በፍቅር፣ ይቅር በመባባልና የሰለጠነ ፖለቲካን በማራመድ ነዉ። የአንድነት ፓርቲ እያደረገ ያለዉም ይሄንኑ ነዉ።

በዳያስፖራ ያሉ፣ ጥቂት ነገር ግን ድምጻቸዉን በጣም የሚያሰሙ ቡድኖች አሉ። እነዚህ ቡድኖች በአንድ በኩል ከሻቢያ ጋር የሚሰሩ ቡድኖችን በጭፍን ይደግፋሉ። ትላንትና ከኦሮሞ ነጻ አዉጭ ግንባርና ከኦጋዴን ነጻ አዉጭ ግንባር ጋር ተፈጠሮ የነበረዉንና አሁን የሞተዉን፣ የኢትዮጵያ አንድነትን ያልተቀበለዉንና ያላረጋገጠዉን፣ ኤ.ኤ.ፍዲ (ትብብር ለነጻነትና ለዲሞክራሲ) ከመደገፍም አልፈዉ የሚቃዋወሙትን ሲያወግዙ የነበሩ ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የአንድነት ፓርቲ ድንኳኑን በማስፋቱና እነ አቶ ስዬን በማስገባቱ ጠንካራ ተቃዉሞ ሲሰነዝሩ ይሰማሉ። ከነዶር መራራ ጉዲና ጋር አብሮ በመሆን የተቋቋመዉንና በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዓላዊነት ላይ የጸና አቋም ያለዉን መድረክን ይቃወማሉ።

የሚያስደስተዉ ነገር ቢኖር ግን የአንድነት ፓርቲና እንዲሁም መድረክ ከገዢዉ ፓርቲ በአንድ በኩል የሚደርስበትን ጫና ችሎ፣ በሌላ በኩል ከላይ ባነሳኋቸዉ ከተቃዋሚ ወገን ነን በሚሉ የሚደርስበትን ታቃዉሞ መክቶ ጠንካራ የፖለቲካ ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል።

መድረኩ ዉስጥ ባሉ ድርጅቶች ወይንም በመድረክ ስም በአዲስ አበባ፣ በአዋሳ፣ በሆሳእና፣ በባህር ዳር፣ በናዝሬት/አዳማ (ኢሕአዴግ ቢበጠብጥብ ስብሰባዉ እንደተረገ ነዉ የምቆጥርዉ)፣ በመቀሌ፣ በሸሬ፣ በማይጨዉና በአዲግራት ሕዝባዊ ስብሰባዎች ተደርገዋል። በጂማ፣ በድረዳዋ፣ በጎንደር እንዲሁም በተለያዩ የአገሪቷ ግዛቶች ሕዝባዊ ስብሰባዎች በቅርብ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል። አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ማድረግ ያለበትን፣ የትግሉ ባለቤት የሆነዉን ሕዝብ የማደራጀትና ለሙብቱ እንዲታገል የማንቃት ሥራዎች እየተሰሩ ነዉ።

ይህም ሁላችንንም ሊያስደስትና ሊያበረታታ የሚገባ ነዉ። ይህ የአንድነት ፓርቲ እያደረገ ያለዉ እንቅስቃሴ ከግብ እንዲደርስ ከተፈለገም ያላሰለሰ የእያንዳንዳችን ሙሉ ድጋፍ ፓርቲዉ ያስፈልገዋል።

ጎበዝ የአገሬ ልጅ፣ ሕዝባዊዉን እንቅስቃሴ እንቀላቀል። በተለያዩ ምክንያቶች ከትግሉ የሸሸን ወደ ትግሉ እንመለስ። ተስፋ ቆርጠንና ያቀረቀርን ቀና እንበል። ዝምታን የመረጥን እንነሳ። ለልጅ ልጆቻችን የበለጸገችና አንድነቷ የተጠበቀን ኢትዮጵያ እናስረክብ! አሁን ካልተነሳ መቼ ? እኛ ካልተነሳን ማን ?